12/02/2018

<u>የጌታ ምፅዓት</u>



ዛሬ ብዙ መንፈሳዊ  በዓላት የብዙዎች የገቢ ምንጭ፣ ትርፍ ማግኛ፣
የሀገር ኢኮኖሚ መገነቢያ ሆነዋል ቤተ/ክ ደግሞ ተባባሪ ሆናለች።
ወንጌል መሰበክ ቆሟል የጌታ ምፅአት ተረስቷል ጌታ ግን :
ራእይ 22:20፤
ይህን የሚመሰክር፡— አዎን፥ በቶሎ እመጣለሁ፡ ይላል። አሜን፥

ጌታ ኢየሱስ ሆይ፥ ና።
የጌታ ምፅዓት እየቀረበ ባለበት በዚህ በመጨረሻው ሰዓት ቤተ
ክርስቲያን ግን ተኝታለች ተዘናግታለች።
ዮሐንስ 14 (John)
1፤ ልባችሁ አይታወክ፤ በእግዚአብሔር እመኑ፥ በእኔም ደግሞ እመኑ።
2፤ በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፤ እንዲህስ ባይሆን ባልኋችሁ ነበር፤
ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና፤
3፤ ሄጄም ስፍራ ባዘጋጅላችሁ፥ እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ
ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ።
ዮሐንስ 14 (John)
18፤ ወላጆች እንደ ሌላቸው ልጆች አልተዋችሁም፤ ወደ
እናንተ እመጣለሁ።
# ጌታ እንደ ተስፋ ቃሉ ይመጣል ወደ ዘላለም ቤታችንም
ይወስደናል #
??? ምን ያህል ተዘጋጅተናል???
ዛሬ የምናስበው የምንጨነቅበት ነገር ምንድን ነው? አዕምሮአችንን
የተቆጣጠረው መንፈሳዊ ነገር ወይስ የዚህ ምድር ነገር?
ዛሬ ስለወንጌል መከራ ውስጥ ነን ወይስ ስለኑሮ መከራ እያየን ነው???
የእግ/ርን መንግስት የምናፋጥንበት አንዱ መንገድ
ወንጌል መስበክ ነው።
ሐዋ. ሥራ 1 (Acts)
11፤ ደግሞም፦— የገሊላ ሰዎች ሆይ፥ ወደስማይ እየተመለከታችሁ
ስለ ምን ቆማችኋል? ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ
ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት፥ እንዲሁ ይመጣል፡ አሉአቸው።
ኢየሱስ መምጣቱ የማይቀር ነው እንዳረገ ሁሉ እንዲሁ የመለሳል።
ዕብራውያን 10 (Hebrews)
36፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ አድርጋችሁ የተሰጣችሁን የተስፋ ቃል
እንድታገኙ መጽናት ያስፈልጋችኋልና።
37፤ ገና በጣም ጥቂት ጊዜ ነው፥ ሊመጣ ያለውም
ይመጣል አይዘገይምም፤

# ወንጌል ዋጋ የሚያስከፍልበት ዘመን ላይ ነን ያለነው ፣ይህም ቢሆን ግን የሚመጣብንን መከራ በመቀበል ለወንጌል ስራ መትጋት አለብን።
2 ጢሞቴዎስ 4 (2 Timothy)
5፤ አንተ ግን ነገርን ሁሉ በልክ አድርግ፥ መከራን ተቀበል፥ የወንጌል ሰባኪነትን ሥራ አድርግ፥ አገልግሎትህን ፈጽም።
#በምድር ያለነው ለወንጌል ስራ ነው! መንም ምርጫ የለንም።
<u>ለምንድን ነው ጌታ እስከ ዛሬ ጌታ ያልመጣው???</u>
እመጣለሁ ካለ ብዙ ዘመን አልፏል ፣ነገር ግን ዛሬም አልመጣም።
በብዙ ስፍራ ይህ ቃል አይነገርም። የእግ/ር ቃል
በ2 ጴጥሮስ 3 (2 Peter)
9፤ ለአንዳንዶች የሚዘገይ እንደሚመስላቸው ጌታ ስለ ተስፋ ቃሉ አይዘገይም፥ ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሣል።
10፤ የጌታው ቀን ግን እንደ ሌባ ሆኖ ይመጣል፤ በዚያም ቀን ሰማያት በታላቅ ድምፅ ያልፋሉ፥ የሰማይም ፍጥረት በትልቅ ትኵሳት ይቀልጣል፥ ምድርም በእርስዋም ላይ የተደረገው ሁሉ ይቃጠላል።
የጌታን መምጣት የምታፈጥነው ቤተ ክርስቲያን ናት ።
ይቀጥላል .......

Last modified: 10:35 PM